# በኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ማዕ/ጎ/ሀ/ስ ለደብረ ኀይል ወደብረ ጥበብ በአታ ለማርያም ካቴድራል የተሰጠ

# የነገረ ቅዱሳን ኮርስ




አዘጋጅ፡- በትረማርያም አበባው ካሣ

(የመጻሕፍተ ብሉያት፣ የመጻሕፍተ ሊቃውንትና የመጻሕፍተ መነኰሳት ትርጓሜ መምህር)


ሐምሌ ፱፣ ፳፻፲፫ ዓ.ም

## ነገረ ቅዱሳን

ይህ ትምህርት ስለቅዱሳን የምንማማርበት ክፍል ነው፡፡ ነገረ ቅዱሳን የወንጌል ገቢራዊ (ሕይወታዊ) ትርጓሜ ነው፡፡

### ቅድስና

ቀደሰ-አመሰገነ፣ ለየ፣ መረጠ ከሚለው የግእዝ ቃል ቅድስና የሚል ጥሬ ምዕላድ ይወጣል፡፡ ትርጉሙ መመረጥ፣ መለየት፣ መመስገን…ወዘተ ማለት ነው፡፡ ቅድስና የባሕርይ ቅድስናና የጸጋ ቅድስና ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡

### የባሕርይ ቅድስና

የባሕርይ ቅድስና ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ይኸውም እግዚአብሔር ቅዱስ ነው ስንል ቅድስናውን ከሌላ ያላገኘው፣ በዘመን ብዛት የማይለወጥ የራሱ የሆነ ዘለዓለማዊ ገንዘቡ ነው ማለታችን ነው፡፡

### የጸጋ ቅድስና

ጸገወ-ሰጠ ከሚለው የግእዝ ቃል ጸጋ የሚል ጥሬ ዘር ይወጣል፡፡ ይኸውም ስጦታ ማለት ነው፡፡ ለፍጡራን ያላቸው ቅድስና የጸጋ ቅድስና ነው፡፡ ይኸውም የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቃቸው፣ ለእግዚአብሔር ተለይተው በመሰጠታቸው ምክንያት የሚሰጥ ነው፡፡ እግዚአብሔር ቸር በመሆኑ ለእርሱ የባሕርዩ ከሆኑት ነገሮች ለፍጡራን ደግሞ በጸጋ የሰጣቸው አሉ፡፡

- ✓ ኢየሱስ ኮከብ እንደተባለ ቅዱሳንም ኮከብ ተብለዋል (ዘኍ.24፥17፤ራእ.22፥16፤ዳን.12፥3)
- ✓ ኢየሱስ መልካም እረኛ እንደተባለ ጻድቃንም መልካም እረኞች ይባላሉ (ዮሐ.10፥11፤ ዮሐ.21፥15-17)
- ✓ ክርስቶስ ብርሃን እንደተባለ ጻድቃንም ብርሃን ይባላሉ (ዮሐ.9፥5፤ ዮሐ.12፥46፤ ማቴ.5፥16)፡፡

ለእግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው ሁሉ የባሕርይ ሲሆን ለሰዎች ለፍጡራን የተነገረው ደግሞ የጸጋ ነው፡፡

### የቅዱሳን ተጋድሎ

ተጋድሎ ማለት ቅዱሳን ስለሃይማኖት ሲያስተምሩ በክፉዎች ነገሥታትና በሐሰተኛ ሰዎች መከራን መቀበል ማለት ነው፡፡ አጋንንትን፣ ነፍስን የሚያውኩ እኩያት ፍትወታትን፣ ኃጣውእን ለመቋቋም ወስኖ በጽናት መጋደልም ተጋድሎ ይባላል፡፡ ቤተክርስቲያን በዓላውያን ነገሥታት፣ በአረማውያን መኳንንት፣ በመናፍቃን ሴራ ስትፈተንና ስትገፋ ብትኖርም እስከዚህ ትውልድ ያደረሳት የእግዚአብሔር ቸርነትና የቅዱሳን ተጋድሎ ነው፡፡

### ቅዱሳን መከራን የሚቀበሉት ከማን ነው?

- ❖ ከፈቃደ ሥጋ (ገላ.5፥16-17)
- ❖ ከዐላውያን ነገሥታት (ማቴ.10፥17-18)
- ❖ ከመናፍቃን (የሐዋ. ሥራ 20፥29-30)

- ከጠንቋዮች (የሐዋ. ሥራ 13፥10)
- ከአሕዛብ (2ኛ ቆሮ.11፥26)
- ከአጋንንት (ኤፌ.6፥10-18)

ቅዱሳን በዚህ ሁሉ ቢፈተኑም እስከሞት ድረስ ለእግዚአብሔር በመታመን ኖረዋል (ራእ.2፥10)።

## ነገረ ቅዱሳንን የመማር ጥቅም

ቅዱስ ጳውሎስ በዕብራውያን መልእክቱ ከአቤል ጀምሮ ያሉትን ቅዱሳን ስማቸውን እየጠራ፣ ታሪካቸውን እየተረከ የስብከቱ አካል አድርጓቸዋል። ወንጌላዊው ሉቃስም ወንጌሉን ሲጽፍ የዘካርያስንና የኤልሳቤጥን ቅድስና በመጥቀስ ነው። በመሆኑም ነገረ ቅዱሳንን መማር ጥቅሙ፡-

- በመልካም ሥራዎቻቸው አርአያ ለማድረግ (ዕብ.13፥7)
- ከቃል ኪዳናቸው ለመጠቀም
- በዘመናቸው ከገጠማቸው ፈተና የወጡበት መንገድ በዘመናችን ለሚያጋጥመን ፈተና መውጫ አርአያ እንዲሆነን

## የቅድስና ዐበይት መሥፈርቶች

ገድላቸውን ለፈጸሙ ቅዱሳን ከዕረፍታቸው (ከሞታቸው) በኋላ ሥራቸው ተመዝኖ መዓርገ ቅድስና ተረጋግጦ ይሰጣል። ይህም በይፋዊ ቀኖና (Official Canonicity) ወይም በትውፊታዊ ቀኖና (Traditional Canonicity) ሊሆን ይችላል። ዋና መመዘኛዎችም የሚከተሉት ናቸው።

- ሃይማኖትን በመጠበቅና በማስጠበቅ ያበረከቱት አስተዋጽኦ
- በገዳማዊ ሕይወት በመጽናት፣ ተአምራትን በማድረግ ያበረከቱት አስተዋጽኦ
- ለእውነት ሰማዕት መሆን
- የተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎቶችን በመፈጸም ያደረጉት አስተዋጽኦ
- እስከ ሕይወታቸው ፍጻሜ ድረስ በጾም፣ በጸሎት ተወስነው በአምልኮተ እግዚአብሔር መጽናታቸው
- የእግዚአብሔርን ቃል ንባብ፣ ትርጓሜ፣ ምስጢር ሳያፋልሱ በማስተማር መጽናታቸው
- በሕይወታቸው ነውር በሃይማኖታቸው ነቀፌታ ያልተገኘባቸው መሆናቸው

## ለቅዱሳን ምን እናደርጋለን?

አንድ ቅዱስ ቅዱስ ተብሎ ከተሰየመ በኋላ የሚከተሉት ነገሮች ይደረጉለታል።

- ሕይወቱ በገድል መጽሐፍ እንዲጻፍ ይደረጋል (ማቴ.26፥13)
- መልክእ ይደረስለታል
- የመታሰቢያ ቀን ይወሰንለታል፣ የመታሰቢያ ሥዕል ይሣልለታል
- ሕንፃ ቤተክርስቲያን በስሙ ይታነጽለታል (ኢሳ.56፥4)
- በስሙ ጽላት ይቀረጽለታል
- በስሙ እንማጸንበታለን
- የተለያዩ መንፈሳዊ ስያሜዎችን እንሰይምባቸዋለን

የጻድቃን መታሰቢያ ለዘለዓለም ይኖራል (መዝ.111፥6)፡፡ የጻድቅ መታሰቢያ ለበረከት ነው (ምሳ.10፥7)፡፡ ቅዱሳንን አክብሮ መቀበል መንፈሳዊ ዋጋ ያሰጣል (ማቴ.10፥40-42)፡፡ ለገድላት፣ ለድርሳናት መጻፍ መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡፡ ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ የቅዱሳን መላእክትንና የቅዱሳን ሰዎችን ክብራቸውን፣ ተልእኳቸውን፣ የተራድኦ ዜናቸውን እንዲሁም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጣቸውን ቃል ኪዳን ይገልጻልና፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር አምላክ ተብሏል፡፡ የእግዚአብሔር አምላክነት የባሕርይ አምላክነት ነው፡፡ ቅዱሳንም በጸጋ አማልክት ይባላሉ (መዝ.49፥1)፡፡ ሊቀ ነቢያት ሙሴም አምላክ ተብሏል (ዘፀ.7፥1)፡፡

## ቅዱሳን

ከፍጡራን ቅዱሳን እየተባሉ ከሚጠሩት መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

- ቅዱሳት መካናት (ቦታዎች)
- ቅዱሳት ጊዜያት (በዓላት)
- ቅዱሳት ንዋያት
- ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ሥዕላት…
- ቅዱሳን መላእክት
- ቅዱሳን ሰዎች

ናቸው፡፡ ቦታዎች ቅዱስ ለመባላቸው ኢያ.5፥13-15 የቆምክበት ስፍራ የተቀደሰች ናትና ጫማህን አውልቅ ተብሎ ተገልጿል፡፡ እንዲሁም ኢየሱስ ክርስቶስ ግርማ መለኮቱን የገለጸበት ደብረ ታቦር ቅዱሱ ተራራ ተብሏል (2ኛ ጴጥ.1፥16-18)፡፡ ይህንን መሠረት በማድረግ ቅዱሳን ተጋድሏቸውን የፈጸሙባቸውን ቦታዎች ቅዱሳት መካናት እያልን እንሰይማቸዋለን፡፡ በተጨማሪም እግዚአብሔርን እንድናከብርባቸው የተመረጡ ጊዜያት ቅዱሳት ይባላሉ (ዘፀ.31፥15)፡፡ ነገረ እግዚአብሔርን የሚናገሩ መጻሕፍትም ቅዱሳት ይባላሉ (2ኛ ጢሞ.3፥15-17)፡፡

## ቅዱሳት ንዋያት

ለቤተ እግዚአብሔር አገልግሎት ተለይተው የሚያገለግሉ ንዋያት ንዋየ ቅድሳት ይባላሉ፡፡ ወደ ቤተ እግዚአብሔር የገባን ንዋይ ቅዱስ ለግል ዓላማ መጠቀም አይቻልም፡፡ ብልጣሶር በቤተ መቅደስ ንዋያት ፈትፍቶ ስለበላባቸው፣ ስለጠጣባቸው መቅሠፍት ደርሶበታል (ፍት.ነገ.1፤ ዳን.5፥2-9፤ ዘዳ.30፥22-29)፡፡

## ቅዱሳት ሥዕላት

በቅዱሳን ስም የተሣሉ፣ ትምህርተ እግዚአብሔርን የሚገልጹ ሥዕላት ቅዱሳት ሥዕላት ይባላሉ፡፡ ልዑል እግዚአብሔር ቀድሞ ለሙሴ በደብተራ ኦሪት በኂሳም ለጠቢቡ ሰሎሞን በቤተ መቅደስ ሥዕለ ኪሩብን እንዲሥሉ አዝዟቸው ነበር፡፡ እነርሱም በሣሉት ሥዕል ፊት ሆነው ወደ እግዚአብሔር ጸልየው ጸሎታቸው ተሰምቷል (ዘፀ.25፥21-22፤ ዘኍ.7፥8-9)፡፡ ይህም በቅዱሳት ሥዕላት ፊት ቆሞ መጸለይ እንደሚገባ ያስተምረናል (ዘፀ.21፥1፤ 1ኛ ነገ.6፥23፤ 2ኛ ዜና 7፥11)፡፡ በሐዲስ ኪዳን የክርስቶስን ስቅለት ለጢባርዮስ ቄሣር ለማሳየት ሐዋርያው ዮሐንስ ሥሎታል፡፡ በዕለተ ስቅለቱ ደሙን ይጠርግበት ዘንድ ቬሮኒካ ሻሽ በሰጠችው ጊዜ የፊቱ ሥዕል በሻሹ ተቀርጿል፡፡ ጥንታዊ ክርስቲያኖች በግበበ ምድር ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን የሚገልጹ ሥዕሎችን ይሥሉ ነበር፡፡ በሥዕል ወንጌልን ማስተማር ይቻላል፡፡ በሥዕል ፊት ሻማ ስናበራ

በሥዕለ እግዚአብሔር ፊት ሲሆን እግዚአብሔር በባሕርዩ ብርሃን መሆኑን ለመግለጽ ነው። ቅዱሳን ቢሆኑ በጸጋ ብርሃን መሆናቸውን ለመግለጽ ነው (ማቴ.5፥14)። በብሉይ ኪዳን መንበሩን የሚሸከሙ ኪሩቤል ሥዕል በቤተመቅደስ እንደነበረ ሁሉ በሐዲስ ኪዳን ደግሞ አምላክን ዘጠኝ ወር ከአምስት ቀን በማሕፀኗ የተሸከመች የድንግል ማርያም ሥዕል በመቅደስ ይቀመጣል።

## ቅዱሳን መላእክት

ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔርን ጸጋ ወደ ሰው፣ የሰውን ጸሎትና መሥዋዕት ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱ፣ ዕረፍታቸው ምስጋናቸው ምስጋናቸው ዕረፍታቸው የሆኑ ረቂቃን ፍጥረታት ናቸው (ዳን.9፥22፤ የሐዋ. ሥራ 10፥4)። ቅዱሳን መላእክት፡-

- ያድኑናል (መዝ.33፥7)
- ይረዱናል (ዳን.10፥21)
- ያማልዱናል (ዘካ.1፥12-17)
- ጸሎታችንን ያሳርጉልናል (የሐዋ. ሥራ 10፥1-4)
- ይዋጉልናል (ራእ.12፥7)
- ይጠብቁናል (መዝ.9፥10-12)
- በንስሓችን ደስ ይላቸዋል (ሉቃ.15፥8-10)
- ይመግቡናል (1ኛ ነገ.19፥1-8)

## ቅዱሳን ሐዋርያት

ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ይሰብኩ ዘንድ በጌታችን በመድኀኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ የተመረጡ 12 ሰዎች ናቸው (ማቴ.28፥20)። ሐዋርያት ብዙ መከራዎችን በመቀበል፣ አይሁድ እያፌዙባቸው፣ እስከ ሞት በመታመን ወንጌልን አስተምረዋል። በሐዋርያት እግር ተተክተው ወንጌልን ያስተማሩ ደግሞ ሐዋርያውያን አበው ይባላሉ።

## ቅዱሳን ሰማዕታት

በዐላውያን ነገሥታት ፊት ቀርበው ሳያፍሩና ሳይፈሩ ስለፈጣሪ የመሰከሩ ሰማዕታት ይባላሉ። ስለሃይማኖታቸው ስለእግዚአብሔር ክብር ብለው ደማቸውን ያፈሰሱ፣ አጥንታቸውን የከሰከሱ፣ ሕይወታቸውን የሰጡ ናቸው። ሰማዕት ማለት ምስክሮች ማለት ነው። በአደባባይ ስለክርስቶስ የመሰከሩ ናቸው። ስለሃይማኖታቸው ሲያስተምሩ በሐሰተኞች ተሰቃይተዋል፣ በከሓድያን እጅ ሞተዋል። ነፍስን የሚወጉ እኩያት ፍትወታትን፣ አጋንንትን፣ ኃጣውእን ለመቋቋም ተጋድለዋል። በሰይፍ ተመትረዋል፣ በመጋዝ ተተርትረዋል፣ በእሳት ተቃጥለዋል፣ ለአናብስት ተጥለዋል፣ በአጠቃላይ በብዙ ስቃያት ተፈትነዋል። ሰማዕታት "ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ" የሚለውን የጌታ ቃል መሠረት አድርገው ስለእግዚአብሔር ለእውነት የኖሩ ናቸው (ማቴ.10፥28)። ሰማዕትነት በሁለት ይከፈላል። እነዚህም አረንጓዴ ሰማዕትነት (Green Martyrdom) እና ቀይ ሰማዕትነት (Red Martyrdom) ናቸው። አረንጓዴ ሰማዕትነት የሚባለው ከውስጣዊ ፈተና (እኩያት ፍትወታትና ኃጣውእ) ጋር የሚደረግ ትግል ነው። ክፋትን፣ ምቀኝነትንና ሌሎችንም ኃጣውእ ለማስወገድ በጽኑ ጾም፣ በጸሎት፣ በስግደት፣ በትሕርምት፣ በንስሓ ሕይወት በመዋጋት የሚደረግ ተጋድሎ ነው። በዚህም ከተድላ ሥጋ ርቀው፣ በትጋሀ ሌሊት፣ በዐቂበ ሕዋሳትና በትሕትና ጸንተው ይኖራሉ። አረንጓዴ ሰማዕትነት ሰማዕትነት ዘእንበለ

ክዕወተ ደም እየተባለም ይጠራል፡፡ ቀይ ሰማዕትነት የሚባለው ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ቤተ ክርስቲያን፣ ስለ መንግሥተ ሰማያት የአካልና የኅሊና ስቃያትን (Physical and mental sufferings) መቀበል፣ የሕይወት መሥዋዕትነትን መክፈል ነው፡፡ ዓመተ ሰማዕታት የሚባለው ከዲዮቅልጥያኖስ ዘመነ መንግሥት (284 ዓ.ም) ጀምሮ የሚነሣ አቆጣጠር ነው፡፡ ከቅዱሳን ሰማዕታት መካከል ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ቅዱስ ፊቅጦር፣ ቅዱስ ገላውዴዎስ፣ ቅዱስ ቴዎድሮስ፣ ቅዱስ አባ ኖብ፣ ቅዱስ አቦሊ፣ ቅዱስ ፋሲለደስ፣ ቅዱስ ሚናስ፣ ቅዱስ ቂርቆስ፣ ቅዱስ አባዲር፣ ቅዱስ መርቆሬዎስ፣ ፴ ሐራ ሰማዕታት፣ ቅዱስ ጎርጎርዮስ ዘአርማንያ ሰማዕት ዘእንበለ ክዕወተ ደም፣ ቅዱስ መርምህናምና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡

## ቅዱሳን አበው

በሕገ ልቡና ፈጣሪያቸውን እግዚአብሔርን ያገለገሉ አባቶች ቅዱሳን አበው ይባላሉ፡፡ ምሳሌ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ ይጠቀሳሉ፡፡

## ቅዱሳን ነቢያት

ቅዱሳን ነቢያት ሀብተ ትንቢት ከእግዚአብሔር ተሰጥቷቸው ባለፈው ዘመን የተደረገውን፣ አሁን ያለውንና ወደፊት የሚመጣውን በእርግጠኝነት የተናገሩና የሚናገሩ ናቸው፡፡ ቅዱሳን ነቢያት ትንቢትን ከመናገር በተጨማሪ በዘመናቸው የነበረውን ንጉሥና ሕዝቡን ያስተምሩ ነበር (2ኛ ጴጥ.1፥21፤ ማቴ.10፥41)፡፡

## ቅዱሳን መነኰሳት

ከሕገ እንስሳ ሕገ መላእክት ይበልጣል ብለው በድንግልና ተወስነው ወይም ዓለምን ንቀው፣ ስለ መንግሥተ ሰማያት ብለው ራሳቸውን ጃንደረቦች ያደረጉ ናቸው (1ኛ ቆሮ.7፥32-34)፡፡ መላ ዘመናቸውን ወይም ከመነኰሱበት ጀምሮ ከጣዕመ ዓለምና ከተድላ ዓለም ተለይተው በምናኔ ጸንተው የኖሩ ናቸው (ዕብ.11፥37-38)፡፡ መነኰስ ማለት ከዓለም የራቀ መናኝ ማለት ነው፡፡ የመነኰሳት ቆባቸው የአክሊለ ሦክ፣ ቀሚሱ የከለሜዳ፣ ቅናቱ የሐብል ምሳሌ ነው፡፡ ምንኵና ሦስት ዓይነት ሥርዓት አለው፡፡

- ✓ ድውይ ዘበአኰቴት፡- ደዌውን በምስጋና የሚቀበል ነው፡፡
- ✓ ባሕታዊ ዘበኀድዐት፡- በጾጥታ፣ በዝምታ፣ በጭምትነት ብቻውን የሚኖር ነው፡፡
- ✓ ረድዕ ዘበጥብዐት፡- ቆራጥ አገልጋይ፣ የራሱን ፈቃድ ትቶ የሌሎችን መልካም ፈቃድ የሚገጽም ነው፡፡

ከቅዱሳን መነኰሳት ጥቂቶቹ አባ እንጦንስ፣ አባ መቃርዮስ ዘየዐቢ፣ አባ ጳኵሚስ፣ አባ መቃርዮስ ዘቆቅሕ፣ አባ ዞሲማስ፣ ዘባ አርሳንዮስ፣ አባ ዮሐንስ ሐፂር፣ ቅድስት ሂላርያ፣ ቅድስት እንባ መሪና፣ ቅድስት ማርያም ግብጻዊት፣ አባ አሞን ይጠቀሳሉ፡፡ በሀገራችን ምንኵናን የመሠረቱትና ያስፋፉት ተስዓቱ ቅዱሳን ናቸው፡፡ ከእነርሱ በመቀጠል በሀገራችን በምንኵስና ከሚታወቁ ቅዱሳን መካከል አቡነ ተክለ ሃይማኖት፣ አቡነ ኤዎስጣቴዎስ፣ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ፣ አቡነ ሳሙኤል ዘዋልድባ፣ አቡነ ዜና ማርቆስ፣ አቡነ ሀብተ ማርያም፣ አቡነ ሊባኖስ፣ አቡነ ሐራ ድንግል፣ አቡነ ተክለ አልፋ፣ አቡነ ኢየሱስ ሞዐና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ አባቶች ከምንኵስና በተጨማሪ ወንጌልን በማስተማር የደከሙ ናቸው፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሐዲስ ሐዋርያ እየተባሉም ይጠራሉ፡፡

## ቅዱሳት አንስት

በፍኖተ ክርስቶስ ተመርተው፣ ቅድስናን ገንዘብ አድርገው ስለክርስቶስ ሰማዕት የሆኑ፣ ይህንን ዓለም ንቀው የመነኰሱና ሌላም መንፈሳዊ ሥራን የሠሩ ሴቶች ቅዱሳት አንስት ይባላሉ፡፡ ፊታውራሪያቸው እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ናት፡፡ ከቅዱሳት አንስት ጥቂቶቹ 36ቱ ቅዱሳት አንስት፣ ቅድስት ማክሪና፣ ቅድስት ክርስቶስ ሠምራ፣ ቅድስት ወለተ ጴጥሮስ፣ ቅድስት ማርያም ግብጻዊት፣ ቅድስት ኢየሉጣ፣ ቅድስት አርሴማ፣ ቅድስት ሶፍያ፣ ቅድስት ፍቅርተ ክርስቶስና ሌሎችም ይጠቀሳሉ፡፡

## ቅዱሳን ጳጳሳት

ምእመናንን፣ ካህናትን ይጠብቁ ዘንድ ቤተክርስቲያንን ያስተዳድሩ ዘንድ የተሾሙ አባቶች ጳጳሳት ይባላሉ (የሐዋ. ሥራ 20፥28)፡፡ ቅዱሳን ጳጳሳት መናፍቃን ሲነሡ ተሰብስበው ትክክለኛውን ሃይማኖት ጠብቀው መናፍቃንን እያወገዙ የኖሩ ናቸው፡፡ በሀገራችን በኢትዮጵያ ሃይማኖትን በማስተማር፣ ሥርዓትን በማጽናት የሚታወቀው የመጀመሪያው ጳጳስ አቡነ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ነው፡፡ ለሃይማኖታቸውና ለሀገራቸው ክብር ሰማዕት የሆኑት ደግሞ አቡነ ጴጥሮስ ናቸው፡፡

## ቅዱሳን ነገሥታት

በሥልጣናቸው፣ በሠራዊታቸው፣ በሀብታቸው ሳይመኩ ሃይማኖትን ይዘው ምግባር ሠርተው የተገኙ ነገሥታት ናቸው፡፡ ትምክህታቸውን እንደ ዳዊት በእግዚአብሔር ላይ በማድረግ ሕይወታቸውን ለእግዚአብሔር በማስረከብ የጸኑ ናቸው፡፡ የሚመሩትን ሕዝብ ፍርድ ሳያጓድሉ፣ ድኻ ሳይበድሉ፣ ጉቦ ሳይቀበሉ፣ ለሰው ፊት ሳያደሉ አስተዳድረዋል፡፡ ለምሳሌ በሀገራችን ከተነሡት ቅዱሳን ነገሥታት የመከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡ አፄ ካሌብ፣ ቅዱስ ላሊበላ፣ ቅዱስ ነአኵቶ ለአብ፣ ቅዱስ ገብረ ማርያም (ሐርቤ)፣ ቅዱስ ይምርሐነ ክርስቶስ፣ አጼ ገብረ መስቀል፣ አብርሀ ወአጽብሐ (ኢዛናና ሳይዛና) ይጠቀሳሉ፡፡

## ቅዱሳን ሊቃውንት

ቅዱሳን ሊቃውንት ቅዱሳት መጻሕፍትን በመተርጎም ምእመናንን በሃይማኖት ያጸኑ ናቸው፡፡ ከሓድያን የተሳሰተ ትምህርት ይዘው ሲነሡም ኀይለ ቃል ጠቅሰው ተከራክረው የረቱ ናቸው፡፡ ሃይማኖት እንዳይጠፋ፣ ትምህርቱም እንዳይፋለስ ሌት ከቀን በማስተማር በርካታ ደቀመዛሙርትን ፈረ፣ አያሌ መጻሕፍትንም የጻፉ ናቸው፡፡ በሀገራችን ከተነሡት ቅዱሳን ሊቃውንት ቅዱስ ያሬድና አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ይጠቀሳሉ፡፡

## የቅዱሳን አማላጅነት

አማላጅ ማለት ስለሌላው የሚጸልይ የሚለምን ማለት ነው (ዘፀ.32፥31-32)፡፡ ቅዱሳን በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን ያገኙ ባለሟሎች ናቸው፡፡ ምልጃን እግዚአብሔር የፈቀደላቸው የፍቅሩ መግለጫ ነው (ያዕ.5፥16-18፤ ራእ.8፥3-4፤ ምሳ.15፥29፤ 2ኛ ቆሮ.9፥13-15)፡፡

## የቅዱሳን ቃል ኪዳን

ራሱ እግዚአብሔር ከመረጣቸው ጋር ቃል ኪዳን እንደሚያደርግ ነግሮናል (መዝ.88፥3)፡፡ እግዚአብሔር በቅዱሳን ቃል ኪዳን ይጠብቀናል (ዘፍ.9፥1)፡፡ የቅዱሳን ሁለንተናቸው የከበረ ነው

(ዘፍ.12፥12)። ስማቸው፣ ጥላቸው፣ ልብሳቸው፣ ዐፅማቸው የከበረ ነው (ዘፍ.12፥12፤ 2ኛ ነገ.13፥20፤ የሐዋ. ሥራ 19፥11-12)። ለቅዱሳን የጸጋ ስግደት ይሰገድላቸዋል (1ኛ ነገ.18፥7፤ 2ኛ ነገ.1፥13)።

## መዓርጋተ ቅዱሳን

መዓርጋተ ቅዱሳን በሦስት ዐበይት ክፍሎች ወይም በዐሥር ንዑሳን ክፍሎች ይከፈላል። በዐቢይ አከፋፈል ንጽሐ ሥጋ፣ ንጽሐ ነፍስ፣ ንጽሐ ልቡና ተብሎ ይከፈላል። በንዑስ ደግሞ ጽማዌ፣ ልባዌ፣ ጣዕመ ዝማሬ፣ አንበዕ፣ ኵነኔ፣ ሑሰት፣ ፍቅር፣ ንጻሬ መላእክት፣ ተሰጥሞ ብርሃንና ከዊነ እሳት ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ንጽሐ ሥጋ፣ ቀጥለው ያሉት አራቱ ነጽሐ ነፍስ፣ በመጨረሻ ያሉት ሦስት ንጽሐ ልቡና ይባላሉ። ዐሥሩ ከነትርጉማቸው እንደሚከተለው ናቸው።

**፩. ጽማዌ፡-** በመናገር ከሚመጣ ኃጢአት ለመጠበቅ ዝም ማለት ነው።

**፪. ልባዌ፡-** ቃለ እግዚአብሔርን ልብ ማድረግ ወይም ማስተዋል ነው።

**፫. ጣዕመ ዝማሬ፡-** ሳይሰለቹና ሳይቸኩሉ ምስጢርና ትርጓሜውን እያስተዋሉ በንቁ ኅሊና ማመስገን ነው።

**፬. አንብዕ፡-** ሰውነት በኀዘን ሳይከፋ የሚፈስ እንባ ነው።

**፭. ኵነኔ፡-** ፈቃደ ሥጋን ለፈቃደ ነፍስ ማስገዛት ነው።

**፮. ሑሰት፡-** ካሉበት ቦታ ሆኖ ጠፈር ደፈር (ግዘፍ ያለው ነገር) ሁሉ ሳይከለክላቸው ካሰቡበት ደርሰው የፈለጉትን ማወቅ ነው።

**፯. ፍቅር፡-** ፍጥረታትን ሁሉ መውደድ ነው።

**፰. ንጻሬ መላእክት፡-** መላእክትን ከነክብራቸው ማየትና ከእነርሱም ጋር ማመስገን ነው።

**፱. ተሰጥሞ ብርሃን፡-** በሚያስደንቅ ብርሃን ውስጥ መዋኘት ነው።

**፲. ከዊነ እሳት (ነጽሮተ ሥሉስ ቅዱስ)፡-** ሥላሴን በዘፈቀደ ማየት ነው።